## የዓለም የንግድ ድርጅት አባል መሆን የሚያስከትለው ውጤት-

### የአቶ ልሳነወርቅ ጎርፉ ኢሳይንሳዊ አቀራረብ ወይስ የኔ „የተዛባ አመለካከት“!

በየካቲ 12 ቀን 2003 ዓ.ም *„የዓለም የንግድ ድርጅት አባል የመሆን ፋይዳቢስነት“* የሚለውን አጭር ሀተታ ጽሁፌን አስመልክቶ አቶ ልሳነወርቅ ጎርፉ ይህ ዐይነቱ አቀራረብ ሰውን ለማደናገር የወጣ ውዥንብር ነዢ ጽሁፍና በጥንቃቄ ያልተጻፈ ነው በሚል በአውራባ ታይምስ መጋቢት 10 ቀን 2003 ዓ.ም ሰፋ ያለ ነቀፌታ አቅርበዋል። በሳቸውም ግምት ፣ ይህ ዐይነቱ የኔ ትንተና በኤክስፐርቶች ያልተደገፈና ፣ የዓለም የንግድ ድርጅት የሚያራምደውን መልካም ተግባር ለማጉደፍ የቀረበ ስለሆነ ዝም ብሎ መታለፍ የለበትም በማለት በድርጅቱ ላይ ያላቸውን መልካም አስተያየት አስነብበውናል።

በመጀመሪያ ደረጃ ፣ ለዚህ ዐይነቱ ትችት አቶ ልሳነወርቅን አመሰግናቸዋለሁ። ማንኛውም ዐይነት አንድን ህብረተሰብ የሚመለከት ጽህፍ ለንባብ ሲቀርብ አንባቢው ጽሁፉን በሳይንስ መነጽር የማመዛዘንና የመተቸት መብት አለው። በተለይም አንድ ጽሁፍ ውዥንብር የሚነዛ ነው ተብሎ ከታመነ ቶሎ ማረም ያስፈልጋል። ትችት የሚቀርብበትም ጸሀፊ ሳያኮርፍ ትችቱ ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን በጥንቃቄ አንብቦ ወይ ማስተባበል አለበት ፣ ካለበለዚያ ደግሞ የቀረበበት ችችት ትክክልና እርማቱንም የሚቀበል መሆኑን ለአንባቢያን ማሳወቅ አለበት። አንድ ህብረተሰብ ትክክለኛ ፈር ሊይዝ የሚችለውና ህብረተሰብአዊ ችግሮችም መፍትሄ ሊያገኙ የሚችሉት በምሁራን ዘንድ የጦፈ ክርክር ሲካሄድ ብቻ ነው። ከግሪክ ታሪክ ጀምሮ እስከ አውሮፓው የህብረተሰብ ግንባታ ታሪክ ድረስ የተካሄደውን እልክ አስጨራሽ ትግል ስንመለከት ፣ ምሁራዊ ክርክርና ትችት ለጤናማ ህብረተሰብ ግንባታ የቱን ያህል ጠቃሚና እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን ነው የምንረዳው። ስለሆነም አቶ ልሳነወርቅን አመስግናቸዋለሁ። ሀተታዬንና አቋሜን የበለጠ ግልጽ እንዳደርግ ረድተውኛል።

ወደ መሰረተ ሃሳቡ ከመግባቴ በፊት ፣ በጽሁፌ ላይ የጠቀስኳቸው ሁለት ግለሰቦችና አንድ የመልዕክተኛ ቡድን ከአሜሪካን ወደ ኢትዮጵያ ስለመምጣቱ ጉዳይ ውሸት እንደሆነና ፣ በሳቸውም አባባል „ቅጥፈት“ መሆኑን ለአንባቢያን አስታውቀዋል። ይህ ጸሀፊ በማንኛውም ረገድ ይሁን የሰዎችን ስም „ለማጥፋት“ የበሬ ወለድ ወሬ የሚያናፍስበት ምንም ምክንያት የለውም። ሁለቱንም ፣ በጽሁፌ ላይ የጠቀስኳቸውን ምናልባትም የኢንዱስትሪና የንግድ ሚኒስተር ባልደረባዎች መፈጠራቸውንም አላውቅም ነበር። በህይወት መኖራቸውንም ለማወቅ የቻልኩት ፣ በጥር ወር 11 ቀን 2003 ዓ.ም ታትሞ በወጣ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ቢዮሜትሪክ ፎቶአቸውንና ስማቸውን ካየሁና ፣ ስለ ዓለም ንግድ ድርጅት የሰጡትን አስተያየት ካነበብኩኝ በኋላ ነው። እዚሁ ጋዜጣ ገጽ ዘጠኝ ላይ ፣ “*በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ሰሞኑን የዓለም ንግድ ድርጅትን አስመልክቶ ስልጠና ተዘጋጅቷል። በስልጠናው ላይ የዓለም የንግድ ድርጅትን ተግባር መሠረታዊ መርህ፣ በድርጅቱ አባል የሚሆኑ ሀገራት የሚሄዱበትን ሂደት እና ኢትዮጵያ አባል ለመሆን የሄደችበትን እና አሁን ያለችበትን ሁኔታ አስመልክቶ በአቶ ወንድ ወሰን ሸዋረጋ ጥናታዊ ጽሁፍ ቀርቧል።*“ ይህንን ለመሳሰሉ ጥናቶች የተለያዩ ስሞች መስጠት ይቻላል። የመጨረሻ መጨረሻ ግን ግንዛቤን የሚያሳድር ጥናት ነው። ወርክ ሾፕ ወይም ሲምፖዚየም ልንለው እንችላለን። ዓላማው ግን አንድ ነው። እንደዚህ ዐይነቱ ጥናት ሲቀርብ ምናልባት አቶ ልሳነወርቅ አዲስ አበባ ላይኖሩ ይችሉ ይሆናል ፤ ካለበለዚያም ባለፈው ሃያ ዐመታት አዲስ አበባ በሁሉም አቅጣጫ እየሰፋ የመጣ የከተማ ጫካ በመሆኑ እዚያ የሚካሄደውን ፣ ከውጭ የሚገባውንና የሚወጣውን ማንኛውም ባለስልጣን ሊያውቅ አይችልም። ስለሆነም ፣ እኔን እንደ ቀጣፊ አድርገው ስሜን ለማጥፋት ያቀረቡት መሰረት የሌለውን አባባል አልቀበለውም። ይህንን እንደገና ለማስተባበል ቢሞክሩ እንኳ አንባቢ ስለዓለም የንግድ ድርጅት ሊማር የሚፈልገው ነገር ላይ የሚጨምሩት አንዳችም ቁም ነገር የለም። ከዚህ በተረፈ ፣ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የአሜሪካንም ልዑካን እንደመጡና ፣ ኢትዮጵያ የድርጅቱ አባል ለመሆን ከፈለገች በተጨማሪ ምን ማድረግ እንዳለባት ሃሳባቸውን ተናግረዋል። ኔው ቢዝነስ ኢትዮጵያ በመጋቢት ወር 2010 የወጣውን የድህረ ገጽ ገለጻ ይመልከቱ ። በስራ መደራረብና በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ጽሁፎች ለማቀረብ ጥድፊያ ሲደረግ አንዳንድ ጥቃቅን ስህተቶች ሊሰሩ ይችላሉ። ይሁንና ግን እንደዚህ ዐይነቱ ጥቃቅን ስህተቶች መሰረታዊና የጽሁፉን ዋና መልዕክት ይዘት የሚያዛቡ አይሆኑም።

በተረፈ ኢትዮጵያ ያመለከተችው እ.አ. አ በ2003 ዓ.ም ነው ፤ ድርድሩ የጀመረው ግን ከሁለት ዐመት በፊት ነው የሚለውን እሳቸውም አምነው ተቀብለውታል። እንዲህ ተብሎ ሲቀርብ ግን ምንም እንዳልተሰራ ለማጋለጥ ሳይሆን ፣ አስፈላጊ ሆኖ ስላላገኘሁት ብቻ ነው። በተረፈ ፣ እንኳን ይህንን የመሰለ ዓለም አቀፋዊ ድርጅት ቀርቶ የአንድ ዕድር አባል ለመሆንም አንድ ሰው አባል ከመሆኑና ከመወሰዱ በፊት ፀባዩ ሁሉ ይጠናል። እንደዚህ ዐይነቱ አሰራር በሌላ መልክም ቢሆን ውሳኔ ሊያገኝ የሚችለው የተወሰኑ ጥናቶች ከተካሄዱና መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ከተሟሉ በኋላ ነው። ይህንን በምሳሌ ማስረዳት ይቻላል። ለምሳሌ አንድ የዓለም የገንዘብ ድርጅት አባል(IMF) የሆነች አገር የውጭ ሚዛን (BOP) ችግር ካለባት ለገንዘብ ድርጅቱ ሌተር ኦፍ ኢንቴንት ትጽፋለች። ድርጅቱ ብድር ከመስጠቱ በፊት የጠየቀችውን አገር የኢኮኖሚ ሆኔታ(Macroeconomics) „ ለማጥናት“ አንድ አጥኚ ቡድን ይልካል። ከሚመለከተው ባለስልጣን ጋር ከተነጋገረ በኋላ በቀረበለት የስታትስቲክስ ማስረጃ መሰረት ተመልሶ የራሱን ጥናት ያቀርባል። በጥናቱም መሰረት ያች አገር የመሸጋገሪያ ብድር ለማግኘት ከፈለገች ምን ምን ማድረግ እንዳለባት „ሃሳብ“ ይቀርብላታል። ለምሳሌ ለሶሻል መስክ የሚወጣውን ድጎማ የመቀነስ ጉዳይ ፣ የአገርን ካረንሲ ከዶላር ጋር ሲወዳደር መቀነስና(Devaluation) የአገርን ገበያ ልቅ ማድረግ...ወዘተ...ወዘተ. የሚቀርቡ ጥያቄዎች ናቸው። ከድርጅቱ የሚቀርብላትን ቅድመ-ሁኔታ ስታሟላ ብቻ ነው የመሸጋገሪያ ብድር የሚሰጣት። እነዚህ ያሰራሩ ሂደቶች(Modalities) ናቸው እንጂ በራሳቸው የዕውቀት መለኪያዎች ወይም ደግሞ የዕውቀት መሰረተ ሃሳቦች አይደሉም። በገንዘብ ድርጅቱና በዓለም የንግድ ድርጅት የሚቀርቡት ጥናቶችና ምን ምን መደረግ እንዳለባቸው የሚያሳዩ „ምክሩና“ ድርድር ሳይንሳዊ ናቸው ማለት አይደለም። የታወቁ የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ መሳሪያዎች ናቸው። በዚህ የምንስማማ ይመስለኛል። የኔን አቀራረብ በሚመለከት ሌሎችም በተመሳሳይ መልክ አቅርበዋል። ስለዚህ የአቶ ልሳነወርቅ ትችት እስከዚህም ድረስ ለአንባቢያን አዲስና ተጨማሪ ዕውቀት ሊሰጠው የሚችለው ምንም ቁምነገር የለም። መከራከር ያለብን ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ብትሆን ጥቅም ልታገኝ ትችላልች ፣ ወይም ደግሞ በሳቸው ዕምነት ወደኋላ የቀረች አገር በመሆኗ የልማት ዕጣ ይደርሳታል አይደርሳትም በሚለው ላይ ነው። በተጨማሪም ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ርስ በርሱ የተሳሰረ የውስጥ ገበያ ልትገነባ ትችላለች ወይ? ወይስ አትችልም በሚለው ላይ ብቻ ነው መከራከር ያለብን። ይህንን ኋላ ላይ እመለስበታለሁ።

የቀድሞውን የዓለም የንግድ ድርጅቱን ጄኔራል ዳሬክተር በሚመለከት ከካፒታል የቀረበላቸውን ቃለ-መጠይቅና የርሳቸውን መልስ በደንብ አንብበውት ከሆነ ሳይንሳዊ ይዘት የሌለው ብቻ ሳይሆን ፣ አሳሳችም ነው። በመጀመሪያ ፣ ኢትዮጵያ የድርጅቱ አባል ባትሆን ምን ይጎድልባታል? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት መልስ ፣ ለህፃን ልጅ እንደዚህ ካላደርግህ ከረሜላ አልሰጥህም ብሎ የማስፈራራት ዐይነት መልስ ነው የሰጡት። ኢትዮጵያ የድርጅቱ አባል ካልሆንሽ ከኛ ጋር የንግድ ልውውጥ ማድረግ አትችይም የሚላት አገር በፍጹም ይኖራል ብዬ አላምንም። የዓለም ገበያ እየተወሳሰበ የመጣና የድሮ ክላሲካል ካፒታሊስት አገሮችን እየበጣጠሰ ወደ እሲያና በተለይም ወደደሮው የሶቭየት ሪፑብሊክ አካባቢዎች ፣ በተለይም ቻይናን የሚያዋስኑ አገሮች ጋር ሰፊ ገበያ የሚመሰረትበት ሁኔታ እየተዘረጋ ነው። በተጨማሪም ፣ የአፍሪቃ ጉዳይ በዛሬው መልኩ ለብዙ ጊዜ ሊቆይ አይችልም። በዓለም ታሪክ ውስጥ ህብረተሰብአዊና የኃይል መሸጋሸጎች ታይተዋል። አንድ ቦታ ላይ ረግቶ የሚቀር ምንም ህብረተሰብ ሊኖር አይችልም። አዳዲስና ውስጠ-ኃይላቸው ከፍተኛ የሆኑ የህብረተሰብ ኃይሎች ብቅ ሲሉ የነገሮችን ዕድገት በሌላ መልክ እንዲመለከቱ በመገደድ ለዕድገት የሚሆናቸውን መሰረቶች የሚጥሉበት ሁኔታ ይፈጠራል። ስለዚህም ኢትዮጵያን የሚያስፈራት ምንም ነገር የለም። በተረፈ ግን ለአንድ አገር ዕድገት ዋናው መሰረት የውስጥ ገበያ በፀና መሰረት ላይ የመገንባቱ ጉዳይ ነው። ከዚህ በተረፈ ሚስተር ማይክ ሙር ስለውድድር የሰጡት መልስና አስተያየት ታሪካዊና ሳይንሳዊ አይደሉም። በታሪክ እንደተረጋገጠው አንድ አገር በአፍላ ወቅት በሯን ለውጭ ንግድ ልቅ ብታደርግ ያሏት ኢንዱስትሪዎች ይዳከማሉ ፤ የመጨረሻ መጨረሻም ከገበያ ይጠፋሉ። የሚስተር ማይክ ሙር አቀራረብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካፒታሊዝም ሲስፋፋ ያለውን ፣ ደካማ አገሮችን የባሰውን የማዳከሙን ውስጠ-ኃይል ያላገናዘበ ኢሳይንሳዊ መልስ ነው የሰጡት። ይህንን በሚመለከት እነ ፕሮፌሰር ሳሚር አሚን ፣ ፕሮፌሰር ጉንደር ፍራንክ ፣ ኢማኑኤልና ሌሎችም የላቲንና የአፍሪካ እንዲሁም የአሜሪካንና የአውሮፓ ምሁራን እጅግ በሚያረካ መልክ በቲዎሪ ብቻ ሳይሆን በኢምፔሪካል ደረጃም አረጋግጠዋል። ሚስተር ማይክ ሙር በሰጡት በእየአንዳንዱ መስመር ላይ ትችት ብሰጥ ቦታ ማጣበብ ብቻ ሳይሆን ፣ አቶ ልሳነወርቅ ላቀረቡት ትችት በቂና አጥጋቢ መልስ ለመስጠት ቦታው አይበቃኝም ፤ ዕድልም

አላገኝም። እዚህ ላይ የሚያሳዝነው ነገር ጠያቂው ጥያቄን በጥያቄ እየጠየቀና የራሱንም አስተያየት በተዘዋዋሪ እያከለበት የሳቸውን መልስ ፋርሽ እንደሆነ ለማሳየት አለመቻሉ ነው።

ወደ አቶ ልሳነወርቅ ፣ ወደኔ ላይ ወዳነጣጠረው ትችት ጋ ልምጣ። በመጀመሪያ አንባቢን እንዲገነዘብልኝ የምፈልገው ፣ የአቶ ልሳነወርቅ ትችት ፣ መሠረታዊ (Fundamental) ፣ ሳይንሳዊና ይዘታዊ (Essential) አይደለም። በአሰራር ቴክኒኮች ላይና በተራ ጥቅም ታገኛለች በሚል ላይ ያተኮረ ፣ ግን ደግሞ በሳይንሳዊ መነጽር ሲመረመር ብዙ ነገሮችን ያላገናዘበና በኢምፔሪካል ደረጃ ያለተረጋገጠ ነው። ትችታቸውን ካነበብኩኝ በኋላ ብዙም ሳላወጣ ሳላወርድ የደረስኩበት ድምዳሜ ፣ የመተንተኚያቸው ዘዴ ኢምፔሪሲስታዊ የሆነና ፣ በኒዎ-ሊበራል የአስተሳሰብ ክልል ውስጥ የሚዳበል ነው። ይህም ማለት ፣ አቶ ልሳነወርቅ ስለ ኢኮኖሚም ሆነ አንድ አገር በንግድ ድርጅቱ ውስጥ ብትገባ ስለምታገኘው ጥቅም ሲያትቱ ከተራ ንግድ ስሌት አሳብ በመነሳት እንጂ ፣ አንድን አገር እንደ ህብረተሰብ በማየትና የሚጎዱሏትን ነገሮች በሰፊው አጥንተው እንደ ህብረተሰብና እንደ አገር እንድተገነባ ከተፈለገ ምን ምን እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው በመገንዘብ አይደለም። ምናልባት በተራ ንግድ አማካይነት አገር በጠንካራ መሰረት ላይ የሚገነባ መስሏቸው ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ፣ መነሻቸው የነ ዓለም የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ የኒዎ-ሊበራል ከቲዎሪ አቀራረብ በመነሳት ነው የሳቸውን ትክክለኛነት ሊያሳምኑን የሚፈልጉት ። የነዚህን ሁለት እህትማማች ድርጅቶች የኢኮኖሚ ፖሊሲና ተግባራዊ በተደረገባቸው አገሮች ያመጣውን ጠንቅ በሚመለከት ሺህ በሺህ የሚቆጠሩ ጥናቶች ቀርበዋል። ወደ ሩቅ ሳንሄድ የሃያ ዐመቱን የኢህአዴግን የኢኮኖሚ ፖሊሲና ውጤቱን መመልከት ይበቃል። ይህንን በሚመለከት ራሳቸው አቶ ልሳነወርቅ እዚሁ ጽሁፋቸው ላይ ሳያውቁት የንግድ ድርጅቱ አባል መሆን ፣ *„በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ላለ በልማት ወደ ኋላ ለቀረ አገር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፣ አዳዲስ ተቋሞችን ለማቋቋምና ህጎችን ለማሻሻል የመሸጋገሪያ ጊዜ ይሰጣል።“* በማለት የኒዎ-ሊበራሊዝምን አስቀያሚ ውጤት ጠቁመውናል። አንባቢያን ይህንን የአቶ ልሳነወርቅን ርስበርሱ የሚቃረንና ምንም ሎጂክ የሌለውን አረፍተነገር ተመልከቱት። የሳቸው መንግስት ስልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ አገሪቱ ልማት በልማት ሆናለች እያለ ነበር ሲያወራልን የከረመው። በጠቅላይ ሚኒስተሩም ሆነ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቱና የዓለም ባንክ ዘገባ የታመነበት ፣ *„የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በጣም በፍጥነት የሚያድግ“* ኢኮኖሚ ነው እየተባለ ነው። በተጨማሪም ይህንን ዘገባም ኢኮኖሚስት የሚባለው መጽሄት ያረጋግጣል። በመንግስታቸውም ሆነ በሁለቱ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ዕድገት በሚያወድሱ ድርጅቶች የተደረሰበት አመኔታ እንደዚህ ከሆነ ፣ አቶ ልሳነወርቅን በትህትና የምጠይቃቸው ጥያቄ ፣ በልማትና በዕድገት መሀከል ያለውን ልዩነት እንዲያብራሩልኝ ነው። በኢኮኖሚ አድጋለች ፣ ነገር ግን በልማት ወደ ኋላ የቀረች አገር ነች የሚባል አገላለጽና አመለካከት ካለ ይህንን ዐይነቱን ምስጢር ለመረዳት እንደገና ወደ ትምህርት ቤት መግባት ሊኖርብኝ ነው ማለት ነው። ለማንኛውም አቶ ልሳነወርቅ ሳያውቁት የመንግስታቸውን ጉድ እያወጡልን ነው። ከዚህ በተረፈ ፣ ኢትዮጵያ የድርጅቱ አባል ካልሆነች በፍጹም ልማት የሚባል ነገር ልታይ አትችልም ማለት ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ምንነትና የአንድ አገር ህዝብ በራሱ ውስጣዊ ፍላጎትና የማሰብ ኃይል ምንም ነገር ሊያደርግ አይችልም እንደማለትና ፣ የአንድን አገር ህዝብ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን የሰው ልጅ እንደመስደብ ይቆጠራል። የሰውን ልጅ የዕድገት ታሪክና ደረጃ ስንመለከት ከምንም ተነስቶ ቀስ በቀስ እያለ መሳሪዎችን በመስራትና ራሱን እንደ ህብረተሰብ በማደራጀት ከእንስሳ በብዙ እጅ እንደሚሻል አረጋግጧል። በኢኮኖሚና በህብረተሰብ ግንባታ ታሪክ ውስጥም ፣ የዓለም የንግድ ድርጅቱ ስሙን በዚህ መልክ ለውጦ ከመቋቋሙ በፊት ከነበረው አጠቃላይ የታሪፍና የንግድ ስምምነት(GATT) በፊትም ቢሆን ብዙ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ፣ በተለይም ከአስራአምስተኛው ክፍለዘመን ጀምሮ ኢኮኖሚያቸውንና አገራቸውን እየገነቡ ሊመጡ ችለዋል። ከዚህም በተጨማሪ ፣ ኢትዮጵያ የድርጅቱ አባል ከሆነች ህጎቿን ለማሻሻል ዕድል ታገኛለች የሚለው አነጋገር ፣ የድርጅቱ አባል ካልሆነች እጅና እግሯን ተብትቦ የያዛት አስማት አይለቃትም ማለት ነው ወይ? የድርጅቱስ አባል ከሆነች የተጋረደው ዐይኗ በመገለጥ ብርሃንን ታጋኝለች ማለት ነው ወይ? የማይገባኝ ሎጂክ!

ሌላው አቶ ልሳነወርቅ ቀደም ብለው ሊያረጋግጡልን የሞከሩት ፣ ኢትዮጵያ የንግድ ድርጅቱ አባል ለመሆን እንዲያበቃት ሁሉንም የህበረተሰብ ክፍል ያካተተና በዓለም አቀፍ ደረጃ በታውቁ ኤክስፐርቶች የተመከረበት ነው ይሉናል። ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ያካተተ ነው ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ሰራተኛውን በሙያ ማህበሩ አማካይነት ፣ ገበሬውን እንደዚሁ በማህበሩ አማካይነትና ሌሎችንም የሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮች ጋር ተወያይተናል ፣ ተከራክረናል ሊሉን ፈለገው ነው ወይ ? በኢትዮጵያ ምድር አንድ ሰው ሃሳቡን በድፍረት ለመግለጽ በማይችልት አገር ፣ የፕሬስ ነጻነት በታፈነበትና እንዲሁም ሰራተኛውም ሆነ ገበሬው ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ ሆነው መደራጀት በማይችሉበት የፖሊስ ስቴት በሚመስል አገር ውስጥ ምን ዐይነት ውይይትና ጥናት ነው የሚካሄደው ? ሊሆን ይችላል ብለን የአቶ ልሳነወርቅን አባባል ብንቀበልም እንኳ ፣ እያንዳንዱ የሙያ ድርጅት የዓለምን ኢኮኖሚ አወቃቀርና ውስጣዊ ህግጋት ሊገነዘብ የሚችልና ሰፊ ጥናት ያጠና ኤክስፐርቶች እንዲኖሩት ያስፈልጋል። ይህንን በሚመለከት ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን ብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ብዙ ችግርች አለባቸው። መሪዎቻቸው እነዚህን ከመሳሰሉ ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር እየተደራደሩ የየአገሮቻቸውን ኢኮኖሚ እንዲንኮታኮት ተግባራዊ የሚያደርጉትን የመረረ ፖሊሲ ዝምብለው ከመቀበል በስተቀር ሌላ ምርጫ እንደሌላቸው ባለፈው ሰላሳ ዐመት የተገነዘብነው ሀቅ ነው። የኢትዮጵያም ዕጣ ከዚህ የተለየ አይደለም። ከዚህ በተረፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ በታወቁ ኤክስፐርቶች ጋር እየተመካከርን ነው የሰራነውና የምንሰራው የሚለው አባባል ፣ የምትሰሩና ምክር የምትቀበሉ ከሆነ አባዛኛዎቹ ኤክስፐርቶች የሎቢስቶች ተወካዮች ናቸው። በዓለም ባንክ ውስጥ ተቀጥሮ ይሰራ የነበረ የሲአይ ኤ ሰው John Perkin የሚባለው ፣ Confession of an Economic Hit Men በሚለው መጽሀፉ ውስጥ የራሱን ርኩስ ስራና ኤክስፐርት ነን እያሉ ብዙ የሶስተኛውን ዓለም መንግስታትንና አንዳንድ ምሁራንን የሚያሳስቱትን ርኩስ ተግባር አጋልጧል። ከዚህ ስንነሳ አቶ ልሳነወርቅ የሚሉን በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ ኤክስፐርቶች ለኢትጵያ የተለዩ ሊሆኑ አይችሉም።

ወደ ሌላው አቶ ልሳነወርቅ ወደሚወነጅሉኝ ጉዳይ ጋ ልምጣ። በሳቸው አባባል *„ዶ/ር ፈቃዱ በጽሁፋቸው ምን ለማለት እንደፈለጉና ሃሳበቸውን በግልፅ ለማስቀመጥ ሲቸገሩ ይስተዋላል። ባለሙያዎች ድርጅቱ በተለይም ያልበለጸጉ አገራት ጠበቃ በመሆን ምርቶቻቸውን „እንዲያራግፉ“ ያመቻቻል ብለዋል ይሉናል። በዓለም ንግድ ድርጅቱ ዙሪያ ዕውቀት ያላቸው የተጠቀሱት ባለሙያዎች ይቅርና በግሉ ዘርፍ የተሰማራው ማንኛውም የንግዱ ህብረተሰብና የሁለት ቀናት የግንዛቤ ማስጨበጫ ያለው የወሰደ አርሶ አደር „ ምርትን ማራገፍ“* (dumping) *በዓለም ንግድ ድርጅት ህግ የሚያስጠይቅ ፣ ይህንን በሚያደርጉ ሀገራት ላይም አስፈላጊውን እርምጃ እንደሚወሰድ ጠንቅቆ ያውቃል።“* በማለት አለማወቄን ለአንባብያን ሊያጋልጡኝ ይፈልጋሉ። አቶ ልሳነወርቅ እዚህ ላይ ያልተረዱት አንድ ነገር አለ። የተጻፈ ህግና የተደነገገ ደንብ ሁሉ ይከበራል ማለት አይደለም። ለምሳሌ በመጽሀፍ ቅዱስ ወይም በወንጌል አስሩ የተከለከሉ „ህግጋት“ አሉ። አትሰረቅ ፣ አታመንዝር ፣ ውሸት አትናገር... ወዘተ የሚሉትን እየጣሰ እንደገና ወደ ቤተክርስቲያን እየሄደ እግዚአብሄርን የሚማጸን አለ። እንደዚሁም ፣ በተባበሩት መንግስታት ቻርተር የሰውን መብት አስመልክቶ የሰፈረውንና ብዙ አባል መንግስታት የተቀበሉትን ፣ ራሳቸው መንግስታት እየጣሱ ህዝቦቻቸውን ያሰቃያሉ። በተጨማሪም ፣ ብዙ የሶስተኛው ዓለም መንግስታት በህገ-መንግስታቸው የሰፈረውን የሰብአዊ መብት መጠበቅና ፣ የፐሪስ ነጻነትንና የሰለማዊ ሰልፍ መብትን ማክበር ጉዳይ ሲጥሱ ይታያሉ። ሌሎች ምሳሌዎችንም መጥቀስ ይቻላል። ወደ ኢኮኖሚ ጥያቄ ላይ ስንመጣ አቶ ልሳነወርቅ አባባሌን ቃል በቃል(Literaly) ነው የወሰዱት። ይህ አጻጻፍ ደግሞ በብዙ ከዚህ ጋር በተያያዙ የኢኮኖሚ መጽሀፎች ውስጥ የሰፈሩና በተግባር የተረጋገጡ ናቸው። እስካሁን ድረስም የዶሀው ድርድር አንድ መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ያልቻለው ፣ የኢንዱስትሪ አገሮች ለእርሻ ምርት የሚሰጡትን ድጎማ እምብዛም ለመቀነስ ባለመፈለጋቸው ነው። ለምሳሌ የአውሮፓው አንድነት ለእርሻና ከእርሻ ጋር ለተያያዙ ነገሮች ስድሳ ቢሊዮን ኦይሮ ባጀት በየዐመቱ ይመድባል። በራሱ የአውሮፓው አንድነት ልቅ የነጻ ገበያ ፖሊሲ አማካይነት የተነሳ ገበሬው ምርቱን ለምርት

ወጪ ከሚያወጣው በታች ነው የሚሸጠው። ይህ እንዳይሆን መንግስትም ሆን የአውሮፓው አንድነት ገበሬውን ይደጉማሉ። የአሜሪካን መንግስትም በየዐመቱ ወደ ዘጠና ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ባጀት በመመደብ ገበሬውን ይደጉማል። ጃፓንም እንደዚሁ። ይህንን አሌ ማለት አይቻልም። ከዚህ በተረፈ ብዙ የአፍሪካ ገበሬዎች ከአውሮፓ በሚላኩ የዶሮ ቅንጣቢዎችና የወተት ዱቄት እየተጠቁ ነው። ለምሳሌ አንዳንድ የጋና ገበሬዎች ለተጠቃሚው የሚቀርብ የዶሮና የእንቁላል እርባታ ለማካሄድ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ገንዘብ ከባንክ ተበድረው በመንቀሳቀስ ላይ እንዳሉ ከሆላንድ በሚመጣ የታሸገ ቅንጣቢ ዶሮ መቋቋም ስላልቻሉ ገበያውን እየለቀቁ እንዲወጡ ተገደዋል። እንዲሁም ፣ ህንድ የንግድ ድርጅቱ አባል ከሆነች በኋላ ትናንሽ ገበሬዎች ከውጭ ከሚመጣው ምርት ጋር ለመወዳደር ባለመቻላቸው ፣ ገበሬው ለዘርና ለማዳበሪያ እንዲሁም ለተባይ ማጥፊያ የወሰደውን ብድር መልሶ ለመክፈል ባለመቻሉ በየዐመቱ ወደ መቶ ሺህ ገበሬ ራሱን ይገድላል። ይህንን በዓለም አቀፍ ኩባንያዎች የተደገፈውን ያገራቸውን የገበያ ወረራ የተመለከቱ ቆራጥ የህንድ ሴቶች ገበሬውን በማደራጀትና በምግብ ራሱን እንዲችል በማድረግ የሚያመረቃ ውጤት እያሳዩ ነው። ለምሳሌ የኒዩክለር ፊዚክስ ምሁርና የሶስተኛው ዓለም ህዝቦች ጠበቃ የሆኑት የፕሮፌሰር ቫንዳና ሺባን ግሩም ስራዎች መመልከቱ ለብዙዎቻችን ትምህርት ሊሆን ይችላል። እኝህ ሴት ምሁር ከሶስት መቶ ሺህ በላይ የሚጠጋ ገበሬ በማደራጀት አዲሱን በስልጣን ላይ ያለውንና ከዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ጋር ያበረውን የህንድ ኤሊት በመቋቋም ላይ ናቸው ። ከዚህ በተረፈ ፣ በአውሮፓው አንድነት በግፍ የሚመረተው ምርት የሶስተኛው ዓለም ገበያ ላይ እንዲራገፍ ወደ ውጭ የሚላከው ከቀረጥ ነጻ ይሆናል። ይህም ማለት የሶስተኛው ዓለም ገበያ ላይ ሲቀርብ ለምርት ማምረቻ ከወጣው ወጪ በታችና ከኤክስፖርት ቀረጥ ነጻ ሆኖ ነው የሚሸጠው። ታዲያ በምን መልክና መንገድ ነው የዓለም ንግድ ድርጅቱ ይህንን ሊቆጣጠርና ሊቋቋም የሚችለው። አቶ ልሳነወርቅ ስንት አዋቂዎች በጥናት የደረሱበትንና እኔም ተመራምሬ የደረስኩበትን ነው ሊያጣጥላሉና ሊያስቁብኝ የሚፈልጉት። ከዚህ በተረፈ ድርጅቱ በሎቢስቶች የተወጠረ ነው። የዓለም አቀፍ የሲቭል ሶሳይቲ ማህበር ይህንን በድርጅቱና በሎቢስቶች መሀከል ያለውን የተመሰጣጠረ ስራ አጋልጧል። በሱም አባባል ፣ “ A Set of manipulative and non-transparent undemocratic processes was planned and used by the WTO Secretariat and major countries to push through the interests of the latter.“ በተጨማሪም በዓለም የታወቁት የስዊዘርላንዳዊ የሶስዮሎጂና የህግ ምሁርና የቀድሞው የተባበሩት መንግስታት ልዩ የምግብ ሪፖርት አጠናቃሪ የነበሩት ፕሮፌሰር ጂአን ሲግለር *„አዲሶቹ የዓለም ገዢዎችና ተቀናቃኞቻቸው“* በሚለው መጽሀፋቸው ውስጥ ፣ የዓለምን የንግድ ድርጅት *„የጦር ማሽን“* የሚል ስም በመስጠት የቱን ያህል በዓለም አቀፍ ኩባንያዎችና በካፒታሊስት አገሮች ቁጥጥር ስር እንደወደቀ በደንብ ይተነትናሉ። እንዲሁም ፣ ብዙ አርቲክሎችንና መጽሀፎችን በመጻፍ የሚታወቀው ፣ ለግሎባል ሪሰርች ተከታታይ ጽሁፍ አቅራቢ ፣ ዊሊያም ኤድጋል የሚባለው አሜሪካዊ ፣ „WTO, GMO and Total Spectrum Dominance“ በሚለው ጽሁፉ ላይ የአሜሪካንን የበላይነትና የዓለም የንግድ ድርጅቱን ለመቆጣጠር የሚደረገውን ጥረት ነው የሚያጋልጠው። በዚህም ምክንያት የተነሳ የአውሮፓ አንድነት ተጠቃሚው ህዝብ በሆርሞን ያደገ የከብት ስጋ ገበያዬ ውስጥ አላስገባም በማለቱ በዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅቱ በተጣለበት ውሳኔ ፣ የአውሮፓው አንድነት ለአሜሪካ በየዐመቱ ቅጣት$ 150 ሚሊዮን ዶላር ይከፍላል። እንደዚሁም ፣ የአውሮፓውን አንድነት ተጠሪዎችና ኮሚሽኖችን የሚያባልጉ ብርሰልስ ብቻ አምስት ሺህ ሎቢይስቶች አሉ። ማንኛውም ህግ ሎቢይስቶች ሳያውቁት አይጸድቅም። በመንግስታትም ደረጃ እንደዚሁ ነው። ስለሆነም የዓለም የንግድ ድርጅቱን እንደቅዱስ አድርጎ መመልከት የዋህነት ብቻ ሳይሆን ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካፒታሊዝም በምን ዐይነት መልክ እንደሚንቀሳቀስ ለመረዳት አለመፈለግ ወይም አለማውቅ ነው። በካፒታሊስት አገሮች የበላይነት ቁጥጥር ስር የወደቀው የዓለም ገበያ እጅግ ውስብስና በቀላሉ ለማንኛውም ተራ ሰው ግልጽ የሚሆን ነገር አይደለም። ይህንን ለመረዳት ወደኋላ ሁለት መቶ ዐመት ተጉዞ ካፒታሊዝም ያለፈባቸውን የዕድገት ደረጃዎችና ዛሬ የደረሰበትን ዕድገት ፣ ደረጃ በደረጃ መመርመርና ማጥናት ያስፈልጋል።

ሌላው የሶስተኛው ዓለም አገሮች ከኮታና ከቀረጥ ነጻ የሆኑ ምርቶች ወደ አውሮፓም ሆነ ወደ አሜሪካና ቻይና እንዲሁም ጃፓን ለማስገባት የአንድ ወገን ችሮታ ተሰጥቷል ይሉናል። አንደኛ ፣ አቶ ልሳነወርቅ እንደሚሉት ምርቶች በቀላሉ ከኮታና ከቀረጥ ነጻ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ቢጻፍም ፣ እዚያው በዚያው ምርቶቹ በገፍ እንዳይገቡ የሚያግዱ ሁኔታዎች አሉ። ለምሳሌ የንጽህና ጉዳይ አለ። ይህንን የማያሟሉ ብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች አሉ። ከዚህ በተረፈ ፣ የአውሮፓው አንድነት ቢሮክራቶች የደነገጓቸው ተፈጥሮን የሚቀናቀኑ ህጎች አሉ። ለምሳሌ የአውሮፓው አንድነት አባል አገሮች ውስጥ የሚገባ ቲማቲም ክብ መሆን አለበት። ሌሎችንም ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ልዩ ዘር መጠቀም ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ ዘሩን ራሷ ለማዳቀልና ለማፍራት ካልቻለች ከውጭ አገር ማስመጣት አለባት ማለት ነው። ከዚህ በተረፈ አቶ ልሳነወርቅ ሊገነዘቡትና በቀላሉ ሊደርሱበት የማይችሉት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ውስጣዊ ህግ አለ። እንደሚታወቀው የሶስተኛው ዓለም አገሮች አባዛኛውን ጊዜ የእርሻ ምርት ውጤቶችን ነው ለዓለም ገበያ የሚያቀርቡት። ብዙዎችም የእርሻ ውጤቶች ያልተፈበረኩ ስለሆነ በዓለም ገበያ ላይ በርካሽ ዋጋ ነው የሚሸጡት። ምክንያቱም ውስጣዊ ይዘታቸው(Valueadded) ከኢንዱስትሪ ምርት ውጤት ጋር ሲወዳደር እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው። ይህም ማለት ለምሳሌ አንድ የሶስትኛው ዓለም አገር አንድ ማሺን ከውጭ ለማስመጣት ብዙ የስራ ጉልበትን ያዘለ ፣ ግን ደግሞ ውስጣዊ ይዘቱ በጣም ዝቅተኛ የሆነ (very low valueadded content) ምርት ማቅረብ አለባት ማለት ነው። በዚህም ምክንያት የንግድ ልውውጡ(Terms of Trade) የሶስተኛውን ዓለም ይጎዳል ማለት ነው። ከዚህ በተረፈ በተለይ እንደ ቡና የመሳሰሉ ምርቶችን ዋጋ የየአገሩ ገበሬና ነጋዴ አይደለም የሚወስነው። የዓለምን ገበያ የሚቆጣጠሩ ኩባንያዎች ናቸው ዋጋን የሚደነግጉ። ክቡር ጌታዩ ነገሩ ውብስብና እኛ ከምንገመተው በላይ  ነው የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ የተዋቀረው። ሌላ የታሪፍ ጣራን ማበጀት የሚለው አባባል ወይም ተቀባይነት ያለው ፣ ኢትዮጵያ የድርጅቱ አባል ሳትሆን ከውጭ ወደ አገር ውስጥ እንደየአስፈላጊነቱ ማሳደግ ትችላለች። ለምሳሌ የራሷን በማደግ ላይ ያሉ ኢንዱስትሪዎችን (Infant Industeries)  ለመከላከል ስትል የኮታም ሆነ የታሪፍ ጣሪያ ማድረግ ትችላለች። ይህ ዐይነቱ አሰራር በታሪክ የተሰራበትና ለዕድገትም ጠቃሚ የሆነ አንደኛው ዘዴ እንደነበር በኢኮኖሚ መጽሀፍ ውስጥ በዝርዝር ተቅምጧል። በነገራችን ላይ ከአስር ዐመት በፊት የኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅና ጫማ አምራቾች ማህበር ተጠሪዎች አቶ መለስ ጋ ሄደው ከቻይናና ከሌሎች አገሮች የሚገቡት ምርቶች ገደብ እንዲደረግባቸው ቢጠይቁ ያለንበት ዘመን የነጻ ገበያ ዘመን ስለሆነ ተወዳደሩ ብለው ነው አሹፈው የመለሷቸው። ይህ ዐይነቱ ፌዝ እያለ ፣ በጊዜውም የኤህአዴግ መንግስት የአገርን አምራች ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ሲችል ፣ አሁን የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ከሆን በነሱ ቡራኬ እማካይነት የታሪፍ ጣሪያና የኮታ ገደብ ለማድረግ እንችላለን የሚለው አባባል እንደማፌዝ ነው የሚቆጠረው።

ከዚህ በተረፈ ግን ክቡር አቶ ልሳነወርቅ እንደካምቦዲያንና ኔፓልን እንደምሳሌ ሲወስዱና ኢትዮጵያም ልታደርግ የምትችለውን የታሪፍ ጣሪያ ፣ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከፍና ዝቅ ማድረግ ሲያወሱ ያላጤኑት እጅግ ጠቃሜ ነገር አለ። በመጀመሪያ ደረጃ ፣ እነዚህ ይህንን የታሪፍ ጣሪያ ዕድል ያገኙ አገሮችን የኢኮኖሚ ሁኔታ ስንመለከት አጠቃለዩ ኢኮኖሚያቸው በፍጹም የሚያመረቃ አይደለም። ስለተራ ንግድና ስለ አንድ ውስጠ-ኃይሉ ከፍተኛ የሆነና በሳይንስና በቴክኖሎጂ ተደግፎ በሚንቀሳቀስ ኢኮኖሚ መሀከል የሰማይና የመሬትን ያህል ልዩነት አለ። አንድ አገር ከውጭ አገር ማሺኖች አምጥታ የተወሰኑ ምርቶችን አምርታ በዓለም ገበያ ላይ በማቅረብና ፣ በሳይንስ ምርምር ውጤት ራሷ ቴኮኖሎጂዎችን ፈጥራ የምታመርተው ምርት ኢኮኖሚያዊና  የማባዛት(Multiplier effect) ኃይሉ እንደዚሁ የሰማይንና የምድርን ኃይል ልዩነት አለ። በሁለተኛ ደረጃ ፣ ስለ እንደዚህ ዐይነቱ በታሪፍ ጣሪያ ሰለሚገኝ ጥቅም ሲወራ ስለ አንድ ንዑስ-መስክ(Sub-sector) ወስደን ብቻ የምናጋንን ከሆነ ስለ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ያለን ግንዛቤ በጣም ዝቅተኛ ነው ማለት ነው። ምክንያቱም ከሌሎች መስኮች ጋር በብዙ ሺህ ድሮች ያልተሳሰረ መስክ ለጠቅላላው ኢኮኖሚያዊ ክምችት(National Capital Accumulation or National Wealth) የሚያበረክተው አስተዋጽዖ በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ ነው። በሶስተኛ ደረጃ ፣ እነዚህን

የመሳሰሉ ፋብሪካዎች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩትን ሰራተኞች ተጨባጭ ደሞዝና ዕድገቱንም መመልከት ያስፈልጋል። በሚያገኙት ደሞዝ በአገር ውስጥ የሚመረተውን ማንኛውም ምርት ገዝተው ሊጠቀሙ ይችላሉ ወይ? ወይስ በትናንሽ ገበሪዎች ከሚመረተውና በገበያ ላይ የሚቀርበውንና በኢንፎርማል መስክ ብቻ የሚመረተውን ምርት ብቻ ነው ገዝተው ሊጠቀሙ የሚችሉት? የሚለውን ማጤኑ ስለ ኢኮኖሚ ዕድገት ያለንን የተጣመመ አስተሳሰብ እንድናስተካክለው ይረዳናል። አቶ ልሳነወርቅ ብዙ ያነሷቸው ፣ ግን ደግሞ ጠቃሚ ያልሆኑ ነግሮች ስላሉ በነሱ ላይ ልረባረብና አንባቢን ለማስልቸት አልፈልግም። ይሁንና ግን አንባቢ በእኔና በሳቸው መሀከል ያለውን ልዩነት እንዲገነዘብልኝ ከቲዎሪና ከታሪክ አንፃር አንዳንድ ነገሮችን ማንሳት እፈልጋለሁ። በተለይም አቶ ልሳነወርቅ *„ሀገራዊ ጥቅምን ባስጠበቀ መልኩ“* ለሚለው አባባላቸው ከታች በአጭሩ የማትተው ቴዎሪ እሳቸው እንደሚገምቱት የሀገርን ጥቅም ማስጠበቅ እንደማይቻል ግልጽ ያደርግልናል። ሀገራዊ ጥቅም ሳይንሳዊ ግንዛቤ እንዲያገኝ ከተፈለገ ከዓለም የንግድ ድርጅቱ ፣ ከዓለም የገንዘብ ድርጅትና ከዓለም ባንክ የኒዎ-ሊበራል ቲዎሪ ባሻገር ማሰብ መቻል አለብን። ይህ ደግሞ ፍልስፍናን ፣ ሳይንስን ፣ ሊትሬቸርን ፣ አርክቴክቸርንና ሌሎች ለተሳሰረ የአገር ግንባታ የሚስያስፈልጉ ነገሮችን ያካተተ መሆን አለበት።

የውጭን ንግድንና የዓለም አቀፍ የስራ ክፍፍልን አስመልክቶ በአስራስምንተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ፣ በተለይም የጀርመን የክላሲካል ኢኮኖሚ ምሁሮች የእነ አዳም ስሚዝንና ሪካርዶን ቲዎሪ በማንሳትና አሳሳች መሆኑን በማመልከት ጠቃሚ ትምህርት ጥለው ሄደዋል። ይህንን የምልበት ምክንያት የንግድ ድርጅቱም ሆነ ሌሎች ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች የእነ አዳም ስሚዝንና የኒዎ-ክላሲካል አሳሳች ቲዎሪን መሰረት አድርገው ስለሚሰሩና ስለሚስብኩ ነው። በአዳም ስሚዝና በሪካርዶ ዕምነት መሰረት በዓለም ንግድ ውስጥ የሚሳተፉ አገሮች ሁሉ እንደተፈጥሮ ሀብታቸው ሁኔታ ቢሰለጥኑ የበለጠ ጥቅም ያገኛሉ ይላሉ። ለምሳሌ ካፒታልና ዕውቀት ያላቸው አገሮች በቴክኖሎጂ ላይ ማትኮር ሲገባቸው ፣ የጥሬ ሀብትና የእርሻ ምርት ማምረት የሚችሉ አገሮች ደግሞ እንደዚሁ በዚያ ላይ ቢያተኩሩና የንግድ ልውውጥ ቢያደርጉ ሁለቱም አገሮች ተጠቃሚ ይሆናሉ ይላሉ። ለምሳሌ እንግሊዝንና ፖርቱጋልን በመውሰድ በአስራስምንተኛው ክፍለዘመን ሁለቱም አገሮች ጨርቅና ወይን ያመርቱ ነበር። ለማምርቻ የሚወጣውንም ወጪ ያወዳድራሉ። ስለሆነም ይላሉ ፣ እንግሊዝ በጨርቃ ጨርቅ ምርት ላይ ብታተኩርና ፣ ፖርቱጋል ደግሞ በወይን ምርት ላይ ብትሰማራና ሁለቱም የንግድ ልውውጥ ቢያደርጉ ፣ በሚቆጠቡት የማምርቻ ዋጋ ጥቅምን ያገኛሉ ይላሉ(Comparative Cost Advantage)። በጊዜው ፖርቱጋል ሁለቱንም ምርት በማምረት ከእንግሊዝ ጋር ስተወዳደር በማምረቻ ዋጋ ወጪ የተሻለ ቦታ ነበራት። ይሁንና የእነ አዳም ስሚዝን ምክር በመቀበል ፖርቱጋል የጨርቃ ጨርቅ ምርቷን በመተው በወይን ምርት ላይ ታታኩራለች።ገበሬውም ለምግብ የሚሆነውን ስንዴና ሌሎች ሰብሎችን ማምረቱን ትቶ የውጭ ከረንሲ ለማግኘት ሲል ወደ ወይን ምርት ላይ ይሰማራል። እንደተጠበቀው ግን የዓለም ገበያ ብዙ የውይን ምርት ውጤትን ሊጠይቅ አልቻለም። ገበያው እየተዳከመ ሲመጣ የፖርቱጋል ገበሬም ገቢ በጣም ይቀንሳል። ለምግብ የሚሆነውንም እርሻ ስለተወ በጊዜው ፖርቱጋል ውስጥ ትልቅ ረሀብ ይከሰታል። ይህ ተረት ተረት ሳይሆን ሀቅ ነው። እነ አዳም ስሚዝ ይህንን የመሰለ አሳሳች ቲዎሪና ፣ ዛሬ በብዙ ዩኒቨርሲቲዎች እንደመጽሀፍ ቅዱስ የሚሰጠውንና የሚደገመውን ቲዎሪ ሲያዳብሩ ከእንግሊዝ ጥቅም በመነሳት ነው። የእንግሊዝን የበላይነት የሚቀናቀኑ ሌሎች አገሮች መውጣት የለባቸውም።

ከላይኛው የሰፈረው ሀተታ በመነሳት በጠቅላላው የእንግሊዝን ኢኮኖሚ የበላይነት ያጠናው የጀርመኑ ብሄራዊ ኢኮኖሚስት ፍሪድሪሽ ሊስት የእነ አዳም ስሚዝን ትምህርትና ምክር እጅግ አሳሳችና አደገኛ መሆኑን ያመለክታል። በሱና እሱን ፈለግ አድርገው በተነሱ ምሁራን ዕምነት ለአንድ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት እርሻ ሳይሆን ፣ ማኑፋክቱርና በዚህ ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ብቻ መሆኑን በማመልከት የጀርመንን ዕድገት ፈለግ ይቀዳሉ። ከዚያ በፊት ጀርመንም ሆነ ፈረንሳይ ከእንግሊዝ ጋር የንግድ ስምምነት አድርገው ጉዳት ስለደረሰባቸው ስምምነቱን በማፍረስ ወደ ውስጥ ያተኮረ የኢኮኖሚ ዕድገት ማካሄድ ይጀምራሉ። በመሆኑም ጀርመን የፍሪድሪሽ ሊስትን ምክር በመከተል በአጭር ጊዜ ውስጥ እንግሊዝን ቀድማ መሄድ ቻለች። አሜሪካንም በአነ ሃሚልተን ዘመን

ይህንን ፈለግ ነው የተከተልቸው። እንደዚህ ዐይነቱን የኢኮኖሚ ዕድገት በሚመለከት በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁት የሀርቫርድ ዩኒቨርሲት ምሩቅና የአማራጭ ኖብል ተሸላሚ የሆኑት የኖርዌይ ተወላጅ ፕሮፌሰር ኤሪክ ራይነርት እጅግ ግሩም በሆነው መጽሀፋቸው *“ ለምን ሀብታም አገሮች ሀብታም ለመሆን በቁ ፣ ለምንስ ደሀ አገሮች በድህነት ላይ ቆመው ቀሩ“* በማለት በሰፊው ያብራራሉ። በእሳቸውም ዕምነት የእርሻ ምርት ውጤት በየጊዜው እየቀነሰ **( decreasing returns)** የሚሄድ ሲሆን ፣ በኢንዱስትሪ ላይ የተገነባ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውጤት እያደገና( increasing returns) ለእርሻም ዕድገት መሰረት ሊሆን የሚችል መሆኑን ያመለክታሉ። የንግድ ድርጅቱ አባል መሆን የሚያመጣውን ጉዳት በመጽሀፋቸው ውስጥ በዝርዝር ሲያብራሩ ፣ ጥቅም እናገኛለን ብለው ተታለው የገቡ አንዳንድ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ኢንዱስትሪዎቻቸው እንደፈራሱባቸው በዝርዝር ይገልጻሉ። በእሳቸውና በስዊድናዊ ምሁር በፕሮፌሰ ጉናር ምይራል ዕምነት በብዙ ዩኒቭርሲቲዎች የሚሰጠው የኢኮኖሚክስ ትምህርት አሳሳችና ለዛሬውም የሶስተኛው ዓለም አገሮች ወደ ኋላ መቅረት ምክንያት መሆኑን ያረጋግጣሉ። ፕሮፌሰር ጉናር ምይራል ለስዊድን ኢኮኖሚ መሰረት የጣሉ ታላቅ ሁለ-ገብ ምሁር ናቸው። ሰሞኑን በታወቀው በጀርመን አገር በሚታተም የንግድ ጋዜጣ ላይ የጠቀለላውን የሶስተኛውን ዓለም አገሮች የኢኮኖሚ ሁኔታና ፣ በተለይም አሁን በከፍተኛ ቀውስ የሚገኙትን የግሪክንና የፖርቱጋልን ኢኮኖሚ አስመልክቶ አንድ ጸሀፊ የእነ ፍሪድሪሽ ሊስትን ጠቃሚ ትምህርት አመልክቷል። በተጨማሪም የእነ ፍሪድሪሽ ሊስትን ዕውቀቶች የኒዎ-ክላሲካል ኢኮኖሚክስ እንዴት እንደገፈተረው በሚያሳዝን መልክ ያትታል።።

ከድሮው ስህተት ባለመማር ኢትዮጵያ ወደፊት የዓለም ንግድ ድርጅቱ አባል ትሆናለች በሚል በተለይም በስኳር ምርት ላይ ርብርቦሽ እየተደረገና ለምግብ የሚሆነው ማሳ እየተነጠቀ ነው። የአበባ ተከላና ሌሎች ለዓለም ገበያ ላይ የሚቀርቡ የእርሻ ምርት ላይ መረባረብ ሀብትን ማበላሸት ብቻ ሳይሆን ወደፊት ለህዝብ ምግብ የሚሆነውንና የሚቀርበውን ሰብል በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳዋል። ከዚህም በላይ ለውጭ „ኢንቬስተሮች“ የሚሰጠው ሰፋፊ የእርሻ መሬት ረሀቡንና የህዝባችንን በውጭ ዕርዳታ ጥገኝነት የባሰውኑን ያጠነከርዋል። እኛም ይህንን እያየን ባይ ባይ ኢትዮጵያ እንላለን። ከዚህ በመነሳትና ጠቅላላውን የአገራችንንም ሆነ በካፒታሊስት አገሮች ቁጥጥር ስር የወደቀውን የዓለምን ኢኮኖሚ ስንመረምር ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅቱ አባል ብትሆን ተጠቃሚ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሆን ፣ የተወሰነው ነጋዴና ሰፋፊ የእርሻ ምርትን የሚቆጣጠረውና ከዚህ ጋር በሺህ ድሮች የተቆላለፈው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኤሊት ነው። አገራችን ሀብታምና ደሀው የሚፋጠጡባት አገር ብቻ ሳትሆን ፣ ወደፊትም ዘረኝነት የሚስፋፋበት አገር ትሆናለች። አሁንም ባይ ባይ ኢትዮጵያ እያልን ወደማይቀረው ዓለም እንሄዳልን ማለት ነው።

**ፈቃዱ በቀለ**